- 2 -

ሰዎች ከተለያዩ በኋላ መልሰው ይገናኙ ይሆን?

መለያየት ከባድ ነው። የሚፈልጉትን ማጣት ደግሞ ከዚያ ይብሳል። ከጥቂት ሣምንታት በፊት "ሰዎች ለምን ይለያያሉ?" ተብዬ ተጠየቅኩ። መልሱ በሕይወቴ ውስጥ ጥልቅ ወደ ሆነው እውነታ እና ትግል ውስጥ ከተተኝ። በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ መገረም ውስጥም አስገባኝ "ሰዎች ከተለያዩ በኋላ ዳግም ይገናኙ ይሆን?" አንድ የምንወደው ነገር ከተወሰደብን በኋላ ዳግም እናገኘው ይሆን? ማጣት በርግጥ ዘላለማዊ ነውን? ወይንስ ከዚያ ከፍ ላለ ጉዳይ ለማግኘት የተደረገልን ሰበብ ነው? ማጣት በራሱ መጨረሻ ነውን? ወይንስ ለልባችን ህመም መጠገኛ ጊዜያዊ ህክምና ነው?

ስለዚህ ዓለም ስናስብ የሚያስደንቀን አንድ ነገር አለ። ለአንድ ህመም መንስኤ የሆነ ነገር በሌላ መልኩ ደግሞ ፈውስ የሚኝበት መሆኑ ነው። በዚህ ዓለም ቋሚና ዘላለማዊ የሆነ ምንም ነገር የለም። ይህን ስንል ምን ማለታችን ነው? ይህ ማለት ዛሬ በአበባ ማስቀመጫዬ ውስጥ ስለመልካም መዓዛዋና ውበቷ ብዬ ያስቀመጥኳት ፅጌረዳ ነገ ትጠወልጋለች ማለት ነው። ወጣትነቴ ጥሎኝ ይሄዳል። ዛሬ የተሰማኝ የሐዘን ስሜት ነገ አይኖርም። ህመሜም ይወገዳል። ሳቅና ፍንደቃዬም ዘላለማዊ አይደለም። እንባዬም እንዲሁ። ይህ ዓለም ፍፁምነት ባህሪው አይደለም። ፍፁም በሆነ መልኩ ጥሩ ዓለም አይደለም። እንዲሁ ፍፁም በሆነ መልኩ መጥፎ ቦታም አይደለም። ሁለቱንም አይደለም። አላህ ሱ.ወ. በተከበረው መጽሐፉም የሚነግረን ይህንን ነው፡-

﴿إِنَّ مَعَ ٱلۡعُسۡرِ يُسۡرٗا﴾

«ከችግርም ጋር ምቾት አልለ።» (አል-ኢንሺራሕ ፡ 5)

እየበሰልኩ ስመጣ ነበር ይህን አንቀፅ በተሳሳተ መንገድ ተረድቼው እንደነበር የተገነዘብኩት። እገነዘብ የነበረው "ከአስቸጋሪ ሁኔታዎች በኋላ ምቾት" የሚመጣ መሆኑን ነበር። በሌላ አገላለፅ "ሕይወት በአስቸጋሪ ጊዜያትና በመልካም ጊዜያት የተሞላች ናት።" ብዬ አስብ ነበር። ከመጥፎ ጊዜያት በኋላ ጥሩ ጊዜያት ይመጣሉ ብዬ እረዳ ነበር። ይህ የማስበው የዚህ ዓለም ሕይወት አንድም ሙሉ በሙሉ ጥሩ ወይም ደግሞ ሙሉ በሙሉ መጥፎ ነው ብዬ ነው አስብ የነበረው።

ግና የአንቀፁ ትርጉም እንደዚያ አልነበረም። የአንቀፁ ትርጉም 'ከከባድ ሁኔታዎች ጋር ምቾት' ያለ መሆኑን ነው የሚያመለክተው። ከባድ ሁኔታዎችና ምቾቶች አንድ ላይ የሚከሠቱ መሆኑን ነው። ይህም ማለት በዚህ ዓለም ሕይወት ውስጥ ሁሌም ጥሩ፤

ሁሌም መጥፎ ነገር የለም ማለት ነው። በመጥፎ ሁኔታ ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ እንኳ በውስጥ የምናመሰግንበት ሁኔታ ይኖረዋል። በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ስናልፍ ያንን የምንቋቋምበትን ጥንካሬ እና መቻልን አላህ (ሱ.ወ.) ይሠጠናል። መታገስን እንታደላለን።

በሕይወታችን ውስጥ የሚከሰቱ አስቸጋሪ ጊዜያትን ለማጤን ብንሞክር በመልካም ነገራት የተሞሉ የሆኑ ልቦችን እናገኛለን። ጥያቄው ግን፡- ትኩረት ማድረግ የመረጥነው የትኛው ላይ ነው? የሚለው ነው። ችግሩ እኛን ጠልፎ የጣለን የውሸት መረብ ስር የሰደደ መሆኑን ነው። በዚህ ውሸት ማመናችን ሕይወት ያለው ይህ 'ፍፁም መጥፎ" አሊያም "ፍፁም ጥሩ" ነው ብለን እንድናምን አድርጎናል። ይሁን እንጂ ይህ የዚህ ዓለም ተፈጥሯዊ ባህሪ ኢይደለም። የዚህ ዓይነቱ ባህሪ (ፍፁም መጥፎ" አሊያም "ፍፁም ጥሩ") የቀጣዩ ዓለም /አኺራ/ ባህሪ ነው። ቀጣዩ ዓለም የሁሉም ነገራት ፍፅምና ያለበት ነው። ጉድለትና እንከን የሌለበት የተሟላ ዓለም። ጀነት ፍፁም በሆነ መልኩ ምሉዕ ናት። እንከን አልባ ጥሩ ዓለም። በውስጧ ምንም መጥፎ ነገር የለም። ጀሃነም (አላህ ይጠብቀንና) ደግሞ ሙሉ በሙሉ መጥፎ ቦታ ናት። በውስጧም ምንም መልካም ነገር የለም።

ይህንን እውነታ በጥልቀት ባለመረዳት በሕይወቴ ውስጥ በሚከሰቱ መልካምም ይሁን መጥፎ ጊዜያዊ ክስተቶች ተውጬ ነበር። እያንዳንዱን ክስተት ጥልቀት ባለው መልኩ እኖረው ነበር። ልክ ማለቂያ እንደሌለውና ፍፁም እንደሆነ በመቁጠር። አንድን ነገር በምረዳበት ሁኔታ ብቻ ለመላው ዓለምና በውስጧ ላሉ ነገሮች ሁሉ ያለኝን አመለካከት ይቀይረው ነበር። በሆነ ቅጽበት የደስተኝነት ስሜት ከተሰማኝ ያለፈውና የአሁኑም፤ የቅርቡም የሩቁም፤ አጠቃላይ ዓለም ሁሉ ለዚያች ቅፅበት መልካም ሆኖ ይሰማኛል። ፍፅምና የዚህ ዓለም ባህሪ የሆነ ያህል ይሰማኛል። ከመጥፎ ክስተቶች ጋርም የሚሰማኝ እንዲያው ነው የሚሆነው። አሉታዊው ነገር ሁሉንም ነገሬን የመቆጣጠር ሃይል ይኖረዋል። ዓለሜ ሁሉ ይኸው ሀሳብ ይሆናል። ልክ በደስተኝነት ስሜት ጊዜ ሲሰማኝ እንደነበረ ሁኔታ ሁሉ ያለፈውና የአሁኑም፣ አጠቃላዩ ዓለም ክፉና መጥፎ ሆኖ ይታየኛል። ለዚያች ቅፅበት ከዚያ ውጭ ምንም መመልከት አልችልም። የኔ ዓለም ያ ሆኗልና ነው ይህ የሆነው።

ዛሬ ላይ በዚያ አመለካከት ብትተቹኝ ያኔ የነበርኩበትን ዓለም ስለማታውቁ ብቻ ነው። ይህ አመለካከት ነበር ያኔ ሕይወቴን ተቆጣጥሮት የነበረው። ይህ የሆነው ከዚህ ዓለም ፍጽምናን በመጠበቄ ነበር። ይህ ሁኔታ ነበር ውስጤን የተቆጣጠረው።

በሕይወት ልምዳችን ውስጥ ብዙዎቻችን ይህ ሁኔታ ገጥሞናል ብዬ አስባለሁ። መልካም ነገር ያለማየት ችግር። ለዚህም ነው በሐዲሥ ውስጥ እንደተገለፀው "ምንም መልካም ነገር ካንተ አላየሁም።" ብላ እንደምትከድ ሚስት ልንሆን የቻልነው። ብዙዎችቻችን

ይህ ስሜት በዚያች ቅፅበት ውስጥ ሊያጋጥመን ይችላል። በቅጽበቱ በሚሰማን ስሜት ምክንያት መልካምን ነገርን ያለማየት ችግር ነው ችግራችን። በመጨረሻም ያ ስሜት ሁሉ ነገራችን እስኪሆን ድረስ እንኖረዋለን። ያለፈ እና የአሁኑን ነገር ሁሉ በዚያ ውስጥ እናጠቃልለዋለን።

ግና ምንም ነገር ፍፁም ያለመሆኑን የመረዳት እውነተኛ ግንዛቤ እሳቤያችንን ሁሉ ይቀይረዋል። በዚህም የተነሳ ለቅፅበት በሚፈጠሩ ሁኔታዎች ተጋላጭ የመሆናችን ስሜት ይወገዳል። በዚህ ዓለም ላይ ምንም ነገር ዘላቂ አለመሆኑን፤ ምንም ነገር ፍፁምና የተሟላ አለመሆኑን እንገነዘባለን። ከቅፅበታዊ ክስተቶች ወጥተን ሁኔታዎችን በትክክለኛ ምንነታቸው እንድናይ የሚረዳን አላህ (ሱ.ወ.)ነው። ዓለምን፣ ተጨባጭን፣ ያለፈውንና ያሁኑን ብቻ ሳይሆን በብዙ ነገሮች ውስጥ ተሰንቅራ ያለችን አንዲት ቅጽበት የመረዳት ችሮታ ያድለናል። አላፊ እንጂ ዘላለማዊ አይደሉም የሚል ግንዛቤን ይሠጠናል። ሁሉም ያልፋሉ።

ሳለቅስ፣ ሳጣ ወይም ስጎዳ በሕይወት እስካለሁ ድረስ ምንም ነገር ፍፁም ያለመሆኑን እገነዘባለሁ። በሕይወት እስካለሁ ድረስ ነገ አልያም በሚቀጥለው ጊዜ ሌላ ተስፋ አለ። ለውጥ አለ። ማገገም አለ። ዛሬ አጣሁ ማለት እስከዘላለሙ አጣሁ ማለት አይደለም።

ያጣነውን ነገር መልሰን እናገኛለን ወይ? ለሚለው ጥያቄ መልስ ፍለጋ የሚከተሉትን አስደናቂ ምሳሌዎች በጥልቀት አጠናሁ።

1- ነቢዩ ዩሱፍ (ዐ.ሰ.) ከአባታቸው ከተለያዩ በኋላ ወደ አባታቸው ተመልሰዋልን?

2- ነቢዩ ሙሳ (ዐ.ሰ.) በልጅነታቸው ከእናታቸው ከተነጠሉ በኋላ ወደ እናታቸው ተመልሰዋልን?

3- በአላህ ትዕዛዝ መሠረት ልጁን በረሃ ላይ ጥላ የሄደችው የነቢዩ ኢብራሂም (ዐ.ሰ.) ባለቤት ሃጀር ወደ ባለቤታቸው ኢብራሂም (ዐ.ሰ.) ተመልሳለችን?

4- ጤና፣ ሀብት እና ልጆች የራቋቸው ነቢዩ አዩብ (ዐ.ሰ.) ወደ ሀብታቸው ተመልሰዋልን?

ከነኝህ ሁሉ ታሪኮች ጥልቅ እና ምርጥ ትምህርቶችን እንወስዳለን። በአላህ (ሱ.ወ.) ፈቃድ የተወሰደብን ነገር ሁሉ እንደተወሰደብን አይቆጠርም። ጠፍቷል አይባልም። አላህ (ሱ.ወ.) ዘንድ ያስቀመጥነው ነገር ሁሉ ቀሪ ነው። ሁሉም ነገር ጠፊ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) በቁርአኑ እንዳለው፡-

﴿ مَا عِندَكُمْ يَنفَدُ ۖ وَمَا عِندَ ٱللَّهِ بَاقٍ ۗ وَلَنَجْزِيَنَّ ٱلَّذِينَ صَبَرُوٓا۟ أَجْرَهُم بِأَحْسَنِ مَا كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ ﴾

«እናንተ ዘንድ ያለው ሁሉ ያልቃል፤ አላህ ዘንድ ያለው ግን (ዘልኣለም) ቀሪ ነው። እነዚያንም የታገሱትን፤ ይሠሩት በነበረው በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን።» (አን-ነሕል ፡ 96)

አላህ ዘንድ የተቀመጠልንን ነገር ሁሉ እንዳጣነው መቁጠር የለብንም። አላህ (ሱ.ወ.) የተሻለውን ነገር ቢያስብልን እንጂ ምንንም ነገር አይወስድብንም። የአላህ መልዕክተኛ ሲ.ዐ.ወ. እንዳሉት-

"ምንንም ነገር ለአላህ ብላችሁ አትተውም፤ አላህ (ሱ.ወ.) በበለጠና በተሻለ ነገር የተካላችሁ ቢሆን እንጂ።" (አሕመድ እንደዘገቡት)

የኡሙ ሰለማን (ረ.ዐ.) ባለቤት አላህ (ሱ.ወ.) አልወሰደውም ፤ በአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሊከሳት ፈልጎ ቢሆን እንጂ።

አንዳንዴ አላህ (ሱ.ወ.) አንድ ነገርን ሊሠጠን የሆነን ነገር ይወስድብናል። በዚህ ጊዜ አንድ ነገር ልብ ማለት ያሻናል። የሱ የ(አላህ ሱ.ወ.) መስጠትና መተካት እኛ በፈለግነውና ባሻነው መንገድ ላይሆን ይችላል። ለኛ መልካም የሆነውን ሁሉ እሱ ያውቃልና። በቁርኣኑም እንዲህ ብሎናል፡-

﴿ وَعَسَىٰٓ أَن تَكْرَهُوا۟ شَيْـًٔا وَهُوَ خَيْرٌ لَّكُمْ ۖ وَعَسَىٰٓ أَن تُحِبُّوا۟ شَيْـًٔا وَهُوَ شَرٌّ لَّكُمْ ۗ وَٱللَّهُ يَعْلَمُ وَأَنتُمْ لَا تَعْلَمُونَ ﴾

«አንዳች ነገርን እርሱ ለናንተ የበለጠ ሲሆን የምትጠሉት መሆናችሁ ተረጋገጠ። አንዳችንም ነገር እርሱ ለናንተ መጥፎ ሲሆን የምትወዱት መሆናችሁ ተረጋገጠ። አላህም (የሚሻላችሁን) ያውቃል፤ እናንተ ግን አታውቁም።» (አል -በቀራህ ፡ 216)

ነገር ግን አንድ ነገር በሌላ ቅርፅ ወይም ባልጠበቅነው መልኩ የሚመልስልን ከሆነ ቀድሞስ ቢሆን ለምን ይወሰድብናል? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ሱብሐነላህ!! ምክንያቱም የሚሰጠን ነገር በማጣት ሂደት ውስጥ ስለሆነ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) አንድን ነገር ይሰጠናል። እናም እሱን (ሰጪውን) ዘንግተን በስጦታው ላይ ጥገኛ እንሆናለን። ገንዘብ ሲሰጠን ጌታችንን ትተን የገንዘብ ባርያ እንሆናለን። ሰዎችን በዙሪያችን ሲሰበስብልን እርሱን (ጌታችንን) ረስተን የሰዎች ጥገኛ እንሆናለን:: አቅምና የማድረግ

ኃይልና ሥልጣን ሲሰጠን በአቅማችን እንተማመናለን። ሰጭውንም እንዘነጋለን። ጤናን ሲሰጠን እንታበያለን። የምንሞት መሆናችንንም እንኳ በጭራሽ እንረሳለን።

አላህ (ሱ.ወ.) እንድን ነገር በሰጠን ጊዜ አሱን (ጌታችንን) በመውደድ ፈንታ በስጦታው ፍቅር እንጠለፋለን። እነዚያን ስጦታዎች ወስደን በልባችን ውስጥ እናኖራቸዋለን። ስጦታው እስኪወሰድብን ጊዜ ድረስም ከነርሱ ጋር ተጣብቀን እንቆያለን። ያለነርሱ መኖር እስከማንችል ድረስም እንሆናለን። እያንዳንዷ ጊዜያችንን እነዚያን ስጦታዎች በመውደድ፣ ለነርሱ በመመራትና እነርሱን በማምለክ እናጠፋለን። በዚህም አላህ ሱ.ወ. የፈጠረልን አእምሮና ልብን ባለቤትነቱን የሌላ አካል እናደርጋለን። ከዚያ ቀጥሎ የማጣት ፍራቻ ጠፍሮ ይይዘናል። ከእጃችን አሳልፈን በልቦናችን ውስጥ ያኖርነው ስጦታን የማጣት ፍርሃት ያባከነን ይጀምራል።ባንድ ወቅት ስጦታችን የነበረው ነገር ኋላ ላይ የገዛ አስር ቤታችን ይሆናል። በእጃችን ማኖር ሲገባን በልባችን በከብር ያኖርነው ነገር፤ የፍርሃታችን መንስኤ ይሆናል። እግርና እጃችንን አስሮ ያስቀምጠናል። ከዚህ ነገር ነፃነታችን የምናውጀው እንዴት ይሆን? ጊዜው ሲደርስ ገደብ አልባ በሆነ ምህረቱ አላህ (ሱ.ወ.) ነፃ ያወጣናል። በገዛ እጃችን በራሣችን ላይ የጫነውን ቀንበር ያወርድልናል። ስጦታውን በመውሰድ ነፃ ያወጣናል!!

ስጦታው በመወሰዱ ምክንያት ነፃ ወጥተን በሙሉ ልባችን ወደ ጌታችን እንመለሳለን። በዚያ የማጣት እና የመፈለግ ሁኔታ ውስጥ እንጠይቀዋለን፣ እንለምነዋለን፣ እንማፀነዋን። እንፀልያለን። በማጣታችን ምክንያት ውጤቱ መልካም ይሆንና የቅንነትና የመተናነስ ደረጃ ላይ እንደርሳለን። የአምላካችን ጥገኛ እንሆናለን። ያን የማጣት ሁኔታ ባይከሠትብን ኖሮ ለዚህ ደረጃ አንበቃም ነበር። በማጣታችን ልባችን ሙሉ በሙሉ ወደሱ ተመለሠች።

ልጅዎ በጣም ሲመኝ የኖረውን መጫወቻ አሻንጉሊት ወይም የቪዲዮ መጫወቻ ለመጀመሪያ ጊዜ ስትሰጡት ምን ይከሰታል? ሙሉ ጊዜውን ከተሰጠው ስጦታ ጋር ያሳልፋል። እና ሌላ ምንም የሚፈልገው ነገር አይኖርም። ምንም ነገር አይታየውም። ሁሉንም ነገር ይረሳል። ማጥናትም ሆነ ምግብ መመገብ አይታየውም። በሚጎዳው ነገር ተሰቦ ይቀራል። ያኔ ምን ታደርጋላችሁ ታዲያ?... ልጆቹን እንደሚወድ ወላጅ ምን ልታደርጉ ትችላላችሁ? በዚያ ሁኔታ ውስጥ ልጃችሁን ትተውታላችሁ? ከመጫወቻው ጋር ትተውታላችሁ?

አይ አትተውትም። ሚዛኑን ይጠብቅ ዘንድ መጫወቻውን መልሳችሁ ትወስዱበታላችሁ።

ልጃችሁ የነገሮችን ቅደም ተከተልና የአስፈላጊነት ደረጃ ማወቅ ሲጀምር፣ ሚዛኑንም ሲጠብቅ፣ አእምሮና ልቦናው ወደ ትክክለኛ ቦታቸው ሲመለሱ ስጦታውን መልሳችሁ

ትሰጡታላችሁ ወይም የተሻለ ስጦታ ትተኩለታላችሁ። በዚህን ጊዜ ስጦታው በእጁ የሚይዘው እንጂ ልቦናው ላይ የሚያኖረው ነገር እንዳልሆነ ይገነዘባል። የስጦታ እውነተኛ ቦታ እጅ እንጂ ልብ መሆን እንደሌለበት ይገነዘባል።

በዚያ ስጦታውን የመውሰድ ሁኔታ ውስጥ አንድ ትልቅ ትምህርት አለ። እሱም እኛ ከርሱ እንድንርቅ ያደረጉንን የወደድናቸውንና ጥገኛ የሆንባቸውን ስጦታዎች በመውሰድ ወደራሱ ይመልሰናል። እሱን እንድናስታውስና በርሱ ላይ ብቻ ትኩረት እንድናደርግ ያደርገናል። ይህ ነው ትክክለኛው ስጦታ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) ሊሰጠን ቢሆን እንጂ ነገሮችን አይዝብንም። አይወስድብንም።

እና መገንዘብ ያለባችሁ ነገር በዚህ ዱንያ የስጦታዎች ሁሉ ትልቁ ስጦታ ወደርሱ መቅረብ መሆኑን ነው። አላህ (ሱ.ወ.) ማሊክ ኢብኑ ዲናርን ሊጠብቀው ሲሻ ሴት ልጁን ወሰደበት። በሌላ ጎኑ ግን ከርሱ ከመራቅ ኃጢአት፣ ከዓለማዊ ሕይወት ኃጢአትና ወንጀል ጠብቆ ከጀህነም እሳት በመጠበቅ ስጦታ ተካለት። እናም ማሊክ ኢብኑ ዲናር ወደ ጌታው በመቃረብ መላ ሕይወቱን አሳለፈ። እናም ዘላለማዊውን ጀነት ከሚያገኙትም ሆነ።

ኢብኑል ቀዩም አላህ ይዘንለትና ይህንን የሕይወት ክስተት "መዳሪጅ አስ-ሳሊኪን" በተሠኘው መጽሐፋቸው ውስጥ እንዲህ አስቀምጠውታል፡-

"መለኮታዊው ድንጋጌዎች ከአማኞች አንፃር ሁሌም በቸርነት የሚገለፁ ናቸው። ምንም እንኳ የሁነቱ ክስተት (የምንፈልገውን እና የተመኘነውን) በማጣት ቅርፅ ቢሆንም፤ አስቸጋሪ ፈተናዎችና መሰናክሎች ቢበዙም ከምህረቱ ነው። አንድ የአላህ ባርያ ህመም እንኳ ውስጥ ቢወድቅ እውነታውና ሚስጢሩ ነፍሱን ለማጥራት እንደሆነ ነው።"

እናም ላነሳነው ጥያቄ "ያጣነውን ነገር ዳግም መልሰን እናገኛለን ወይ?". . . ለሚለው ምላሹም አዎን ነው። ይመለሳል እናገኘዋለን። እዚህም ሆነ እዚያ (በቀጣዩ ዓለም) በተለየና በተሻለ ሁኔታ እናገኛለን። ታላቅ ስጦታ ያለው በመውሰዱና በመስጠቱ ውስጥ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) የሚነግረንም ይህንኑ ነው።

﴿ قُلْ بِفَضْلِ ٱللَّهِ وَبِرَحْمَتِهِۦ فَبِذَٰلِكَ فَلْيَفْرَحُوا۟ هُوَ خَيْرٌ مِّمَّا يَجْمَعُونَ ﴾

«በአላህ ችሮታና በእዝነቱ (ይደሰቱ)፤ በዚህም ምክንያት ይደሰቱ፤ እርሱ ከሚሰበስቡት ሀብት በላጭ ነው፤ በላችሁ።›› (ዩኑስ : 58)